ከኀቦ ዉቃው ጥቅምት 13 2000
ከቫንኩቨር ካናዳ

# ጨረቃ-ድምቡልቦቃ!

ጨረቃ ድምቡልቦቃ
ዓፄ-ቤት ገባች አውቃ
ዓፄ ቤት ያሉ ልጆች. . .
“በረከት ና መለስ”. . .
. . .ፈተጉ፤ፈታተጉ
. . .ሆድ አደር ፈላላጉ
ማር የለበሰውን ኳስ. . .
. . .ወደ ቃሊቲ ለጉ።
ቃሊቲ ያለውማ
ይሄ የትግል አክርማ
“አባ-ነጋ-አባ-ዳማ”
አድብቶ ኖሩአልማ
“ጎህ-ሳይቀድ” በጭለማ
ከ”ሃይሉ” ተደብቆ. . .
. . .ቀለባት ሰው ሳይሰማ
ብርቱካን ጮርቃዋማ
ተሸወደች ስታቅማማ።
የወያኔ ባለ-አደራው፤
በዓለሙ ሁሉ ዘራው፤
“ቂል” ብሎ አዋቀረው፤
ብርሃነንም አስላሰው፤
ቀናንም አጎረሰው፤
ክፍቴንም አስጠቀሰው።
“ነጋ” ቆሎ!. . .መሸ ቆሎ!
ልለምንህ ማሎ! ማሎ!
ክህደት ትተህ ሃቁን ቶሎ!!

ቸር ይግጠመን

ከነ ወቃው